# የሽግግር ዕቅድ ማውጫ መምሪያ

የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
በኋላ ወደ ተገቢው ውጤት እንዲሸጋገሩ ማዘጋጀት



የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካል ጉዳት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የመምሪያውን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የሚከተለውን ይገናኙ፦ Equity Assurance and Compliance Branch, Office of the Deputy State Superintendent for Administration, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, 6th Floor, Baltimore, Maryland 21201-2595፣ ስልክ 410-767-0433፣ ፋክስ 410-767-0431, መስማት ለሚሳናቸው 410-333-6442, www.marylandpublicshools.org።

ይህ ሰነድ ተዘጋጀው በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ (MSDE) ልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች፣ በአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ሕግ (IDEA) በኩል ሲሆን፣ ከዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርትና ማገገሚያ አገልግሎቶች፣ IDEA, ክፍል B፣ ችሮታ ቁጥር *-# H027A090035*በተገኘ ገንዘብ ነው። እዚህ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች በግድ የዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ ወይም የማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትና መርሃ ግብሮችን የሚያንጸባርቁ አይደሉም። የ MSDE ልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች ክፍል ከልዩ ትምህርት መርሃ ግብሮች ቢሮ፣ የልዩ ትምህርትና የማገገሚያ አገልግሎቶች፣ የዩ ኤስ ትምህርት ክፍል የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል።

ይህ ሰነድ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው መጋራት ይችላሉ ሆኖም እባካችሁ ከMSDE፣ የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች የመጣ መሆኑን አስታውቁ።

*James H. DeGraffenreidt, Jr.*
*ሊቀመንበር*
የስቴት ትምህርት ቦርድ

*Nancy S. Grasmick*
የስቴት ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ

*Carol Ann Heath*
ረዳት ስቴት ተቆጣጣሪ
የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች

*Martin O'Malley*
አገረ ገዢ

# የሽግግር ዕቅድ ማውጫ መምሪያ፦
# የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ወደ ተገቢው ውጤት እንዲሸጋገሩ ማዘጋጀት

የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ
የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች
ጃኑዋሪ 2010 ዓ.ም.

# ማውጫ

የሽግግር ዕቅድ ማውጫ የቤት ሰነድን በተመለከተ መረጃ ........ i

የሽግግሩ አጭር መግለጫ ........ 1

በ2004 ዓ.ም. የወጣው የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) ........ 2

ሽግግር ዕቅድ ማውጣት ........ 4

ምረቃ ........ 4

የሜሪላንድ መውጫ ሰነድ ........ 5

መብትና ብቃት ሲነጻጸሩ ........ 6

የሜሪላንድ አዋቂዎች አገልግሎት ድርጅቶች ........ 6

1. የሜሪላንድ እድገት ነክ የአካል ጉዳት አስተዳደር (DDA) ........ 7
2. የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል (DORS) ........ 12
3. DHMH የአእምሮ ጤንነት አስተዳደር ........ 14
4. የሠራተኞች እድገት እና የአዋቂ ትምህርት ክፍል ........ 22

በሽግግር ዕቅድ ማውጣት ላይ ወላጅ የሚጫወተው ሚና ........ 25

በሽግግር ዕቅድ ማውጣት ላይ ተማሪ የሚጫወተው ሚና ........ 26

የሽግግር ሂደትኑ ከድርጅት ጋር ማያያዝ ........ 28

# የሽግግር ዕቅድ ማውጫ የቤት ሰነድን በተመለከተ መረጃ

ከትምህርት ይወጣል/ትወጣለች ተብሎ የሚጠበቅበት ቀን፦ ______________________________

ልጇ የሚወጣው/የምትወጣው፦ _____ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ይዞ/ይዛ ነው

_____ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መርሃ ግብር መጨረሻ የምስክር ወረቀት ይዞ/ይዛ ነው

ልጇ የሚጨርሰው/የምትጨርሰው፦ ______________________________

*(የትምህርት ዘርፍ)*

ልጇ የትምህርት እና የሙያ ዕቅዱን/ዷን የሚያገኘው/የምታገኘው በሚከተለው ቀን ነው፦__________

*(Date)*

ልጇ የመውጫ ሰነዱን/ዷን የሚያገኘው/የምታገኘው በሚከተለው ቀን ነው፦ __________

*(Date)*

የልጇ የሽግግር ዕቅድ ማውጫ የቤት ሰነድ ውስጥ መቀመጥ ያለባቸው ዝርዝር ነገሮች፦

የቅርብ IEP _________

የቅርብ የስነ አእምሮ ግምገማ _________

የቅርብ የትምህርት ግምገማ _________

ደምወዝ የተቀበሉበት ደረሰኝ (ከእያንዳንዱ መሥሪያ ቤት) _________

የማንኛውም ሽልማቶች ዝርዝር*_________

የማንኛውም የእንኳን ደስ ያልዎት ደብዳቤ ግልባጭ* _________

የምስጋና ምስክር ወረቀቶች ግልባጭ* _________

*እነዚህ ነገሮች በግድ ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ መሆን የለባቸውም።

# *የሽግግሩ አጭር መግለጫ*
# *አዋቂ ስንሆን ምን እናደርጋለን?*
# *እዛ የምንደርሰው እንዴት ነው?*

*የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ* ***የሽግግር ዕቅድ ማውጫ መምሪያ*** *የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ልጅዎ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ወደ ተገቢው ውጤት ሽግግር እንዲያደርግ/እንድታደርግ ትኩረት ይሰጣል፣ እንዲሁም ወደሚቀጥለው የሕይወት ደረጃ ለመተላለፍ ዝግጅት ሲያደርግ/ሲታደርግ ድጋፍ ይሰጣል። ሁሉም ተማሪ አንድ ዓይነት ዓላማና ውጤቶች አይኖሩትም። ተማሪዎች በሙሉ የወደፊት ሙያን በተመለከተ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል፣ የሙሉ ጊዜ ሥራም ይሁን የትርፍ ጊዜ ሥራ ወይም ለመሥራት እርዳታ የሚያስፈልገው ዓይነት ሥራም ቢሆን። ተማሪዎች በሙሉ የሥራ ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት የሚያስችሉ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ የሚደረግ ትምህርት ወይም የሙያ ስልጠና ዓላማዎች ሊኖራቸው ይገባል። ልጅዎ የተለየ ለብቻ የመኖር ዓላማዎችም ሊኖሩት/ሯት ይችላል።*

*የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ* (IDEA) *የሕጉ ዓላማ "የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ሁሉ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት የሚሰጥ፣ የግል ሁኔታቸውን የሚያመቻችና ለሥራና በግል ለመኖር የሚያዘጋጃቸው ተገቢ ነጻ የመንግሥት ትምህርት እንዲቀርብላቸው " እንደሆነ ይናገራል። በ*2004 *ዓ.ም. በድጋሚ ፍቃድ የተሰጠው* IDEA *በተለይ የልጆች ሽግግር ዕቅድንና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ውጤቶችን በተመለከተ የተጻፈ ጽሑፍ ይዟል። ተማሪው ዓላማዎቹንና ውጤቶቹን ለማሳካት ሲሠራ/ስትሠራ፣ ተማሪው፣ አስተማሪዎች፣ ወላጆች እና የሕብረተሰቡ አገግልግሎት ሰጪዎች አብረው መስራት እንዳለባቸው ሕጉ ደጋግሞ ያሳስባል። ይህ መምሪያ ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎችና የሕብረተሰቡ አገልግሎት ሰጪዎች በበቂ መረጃ ላይ የተመሠረተ ሽርክና እንዲኖራቸው ይረዳል። በተጨማሪም ይህ መምሪያ በዕቅድ ማውጫ ሂደት ላይ አስፈላጊ የሚሆን መረጃ ለወላጆች እንዲሰጥ የቀረበ ነው።*

*ይህ መምሪያ በሽግግር ዕቅድ ማውጫ ሂደት ላይ <u>በበቂ መረጃ ላይ የተመሠረቱ ሽርክናዎች</u> ለማጎልበት ይረዳል። ከትምህርት ቤት ወደ አዋቂነት ሽግግር በሚደረግበት ጊዜ የተማሪው፣ የቤተሰብ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ትብብር ያስፈልጋል።*

*ይህ መምሪያ የሚከተሉትን ርእሶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ያቀርባል፦*

- በ2004 *ዓ.ም. የወጣው የአእምሮ እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ* (IDEA) *የሽግግር ዕቅድን በተመለከተ ያለው መስፈርቶች*
- *የሽግግር ዕቅድ ማውጣት*
- *የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ እና የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፍጻሜ ምስክር ወረቀት መስፈርቶች*
- *የሜሪላንድ መውጫ ሰነድ*
- *መብትና ብቃት ሲነጻጸሩ*

- የድርጅት አገልግሎቶች
    1. የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል (DORS)
    2. እድገት ነክ የአእምሮና የአካል ጉዳት አስተዳደር (DDA)
    3. የአእምሮ ጤና አስተዳደር (MHA)
    4. የሰው ኃይል መምሪያ፣ ፈቃድ ማውጫና መተዳደሪያ ደንብ - የሠራተኛ እድገት እና የአዋቂ ትምህርት ክፍል
- ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ የሚወሰድ ትምህርት ላይ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ላላቸው የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶችን በተመለከተ መረጃ
- በሽግግር ዕቅድ ማውጣት ላይ ተማሪው የሚጫወተው ሚና
- በሽግግር ዕቅድ ማውጣት ላይ ወላጅ የሚጫወተው ሚና
- በሽግግር ወቅት ማያያዝ

# በ2004 ዓ.ም. የወጣው የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA)

IDEA 2004 ሽግግርን "በውጤት ላይ የተመሠረተ፣ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ወደ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሲዘዋወር ስኬታማ እንዲሆን ዝግጅት ማድረግ፣ የትምህርትና የሥራ ስኬትን ማሻሻል ላይ ያተኮረ ሂደት" ብሎ ይተረጉመዋል። በኦገስት 14፣ 2006 ዓ.ም. የወጡት የ IDEA 2004 ደንቦች እንደሚገልጹት፣ የሽግግር አገልግሎቶች ዓላማ "ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን የግል ጉዳይ ማሟላትና ለቀጣይ ትምህርት፣ ሥራና የግል ኑሮ ማዘጋጀት" ነው።

በመቀጠልም፣ የሽግግር አገልግሎቶች የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ላለው ተማሪ የሚከተሉት ዓይነት የተቀናጁ እንቅስቃሴዎች ናቸው፦

- በውጤት ላይ የተመሠረተ ሂደት፣ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ወደ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሲዘዋወር ስኬታማ እንዲሆን ዝግጅት ማድረግ፣ የትምህርትና የሥራ ስኬትን ማሻሻል ላይ ያተኮረ ሂደት፣ ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ያለ ትምህርትን፣ የሙያ ትምህርትን፣ የተቀነባበረ ሥራን፣ ቀጣይ የአዋቂ ትምህርትን፣ የአውቂ አገልግሎቶችን፣ ለብቻ መኖርን ወይም የማህበረሰብ ተሳትፎን ጨምሮ፣
- በእያንዳንዱ ልጅ የግል ፍላጎት ላይ የተመሠረተ፣ የእያንዳንዱን ልጅ ጠንካራ ጎን፣ ምርጫዎችና ፍላጎቶች ላይ የተመሠረተ፣ እና

- ትምህርትን፣ ተዛማጅ አገልግሎቶችን፣ የማህበረሰብ ልምዶችን፣ የሥራ ልማትንና ሌሎች ከትምህርት በኋላ የሚሆን የአዋቂ ኑሮ ዓላማዎችን ይጨምራል፣ ተገቢ ሲሆን ደግሞ የዕለታዊ ኑሮ ችሎታ ማግኘትንና የሙያ ሥራ ግምገማ።

በሜሪላንድ ውስጥ፣ የሽግግር ዕቅድ ማውጣትና የሽግግር አገልግሎቶች አቅርቦት የሚጀምረው ተማሪው 14 ዓመት ዕድሜ በሚሞላበት የትምህርት ዘመን ነው።

# የሽግግር ዕቅድ ማውጣት

የሽግግር ዕቅድ ማውጣት ዓላማ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ትምህርት እየገፉ ሲሄዱና ዓለም ውስጥ እንደ አዋቂ ሆነው ለመግባት ሲዘጋጁ መርዳት ነው። የአዋቂ እንቅስቃሴዎቹ ከሚከተሉት ውስጥ ማንኛውም አብሮ የተደረገ እንቅስቃሴ ሊሆን ይችላል፦

- መቀጠር
- ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ትምህርት
- የሥራ ቅጥር ስልጠና
- ለብቻ ራስን ችሎ ኑሮ
- የማህበረሰብ ተሳትፎ
- የአዋቂ አገልግሎቶች

ለአንድ ተማሪ የወደፊት ሕይወት የሽግግር ዕቅድ ማውጣት የሚጀመረው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረጉ የሙያ ግንዛቤና የምርመራ እንቅስቃሴዎች ላይ ነው። የልጁ ሙያ ግንዛቤ ላይ ቤተሰቡ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በየቀኑ ወላጆች ስለ ግል ልምዳቸው እየተናገሩ ልጆቻቸውን ስለ ቤተሰብና ስለ ጎረቤት ሙያ ማሳወቅ ይችላሉ።
ዕድሜያቸው 14 ዓመትና ከዛ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) በሚዘጋጅላቸው ጊዜ የሽግግር ዕቅድ ማውጣት የመጀመሪያው ደረጃ ነው። ተማሪው ፍላጎቶቹንና ምርጫዎቹን ለትምህርት ቤቱ ሠራተኛ በመንገር ይጀምርና ከዛ በኋላ፦

1. ተማሪውና የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች በሥራ፣ በከፍተኛ ትምህርት ወይም በሥራ ስልጠና እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ራስን ችሎ በመኖር በኩል የሚጠበቁ ውጤቶች ያስቀምጣሉ። እነዚህ ከሁለተኛ ድረጃ ትምህርት በኋላ የሚመጡ ውጤቶች በዕድሜ አኳያ በተደረጉ የሽግግር ግምገማዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

2. ተማሪው/ዋ ወደ ውጤቶቹ/ቿ በጥሩ መንገድ እንዲያመራ/እንድታመራ በትምህርት ዘመኑ ወቅት የሚያስፈልጉት/ጓት አገልግሎቶች፣ የትምህርት ዘርፍ እና ዓመታዊ ዓላማዎችን የትምህርት ቤት ሠራተኞቹ ዕቅድ ያወጣሉ (ይህ ሁሉ መረጃ IEPው ውስጥ ይገባል)።

3. የተማሪው ፍላጎቶችና ውጤቶች አለመቀየራቸውን ለማረጋገጥ ይህ ሂደት በየዓመቱ ይደገማል። ተማሪው ወደተናገረው ውጤቶች ማምራቱን ለማረጋገጥ IEPውን መቀየር አስፈላጊ ከሆነ ይደረጋል።

# ምረቃ

የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ለማግኘት ብቁ ለመሆን ተማሪዎች ሁሉ ቢያንስ 21 የትምህርት ክሬዲት ማግኘት አለባቸው። አስፈላጊ ከሆነው የትምህርት ክሬዲት በተጨማሪ፣ ተማሪዎች ሁሉ ሰባ አምስት (75) ሰዓቶች የተማሪ አገልግሎት መፈጸም ወይም በአካባቢው የተማሪ አገልግሎቶች መርሃ ግብር ወስደው መጨረስ አለባቸው። የአካባቢው የትምህርት ቤት ሥርዓቶች ተጨማሪ የክሬዲት መስፈርቶች ሊኖራቸው ይችላል ወይም ስቴቱ ከሚጠይቀው መስፈርቶች በላይ የክልሉን መስፈርቶች ሲያሟሉ ዲፕሎማው ላይ የድጋፍ ማረጋገጫ ሊጨምሩ ይችላሉ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክሬዲት ከዋና ትምህርት ዓላማዎች ጋር አብሮ በመሆን ለሁለተኛ ደረጃ ግምገማ (HSA) ፈተና መዘጋጀ የሆኑ

ትምህርቶች ተማሪው እንዲወስድ ያስገድዳል። ክሬዲት ያለው ትምህርት ውስጥ በተመዘገበበት የትምህርት ዘመን ወቅት፣ ተማሪው ተዛማጅ HSA መውሰድ አለበት።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ለማግኘት መስፈርቶቹን ማሟላት የማይችሉ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን እስካሟሉ ድረስ **የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመርሃ ግብር ፍጻሜ ምስክር ወረቀት** ማግኘት ይችላሉ፦

- ከ8ኛ ክፍል ወይም ከተመሳሳይ ዕድሜ በኋላ ተማሪው ቢያንስ ለአራት (4) ዓመት የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ተመዝግቧል፣ እንዲሁም በ IEP ቡድኑና በወላጆች ስምምነት መሠረት፣ የሥራ ዓለም ውስጥ ለመግባት፣ ኃላፊነት ለመውሰድ እና የተሟላ አጥጋቢ ኑሮ ለመኖር የሚያስፈልጉትን በቂ ችሎታዎች አዳብሯል ተብሎ ተወስኗል።

- ከ8ኛ ክፍል ወይም ከተመሳሳይ ዕድሜ በኋላ ተማሪው ቢያንስ ለአራት (4) ዓመት የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ተመዝግቧል፣ የተማሪውን ወቅታዊ የትምህርት ዘመን ሲጨርስም ዕድሜው 21 ዓመት ይሆናል።

# የሜሪላንድ መውጫ ሰነድ

የሜሪላንድ መውጫ ሰነድ የሚመረቁ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በኋላ ወደ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሲተላለፉ መጠቀም የሚችሉት አስፈላጊ የIEP መረጃ የያዘ ሰነድ ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ሥራ፣ ከፍተኛ ትምህርት፣ ድጋፍ ያለው ቅጥር ወይም በማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅቶች በኩል የቀረበ ራስን የቻለ ኑሮ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰነዱ ከሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም ከሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ የመርሃ ግብር ፍጻሜ ምስክር ወረቀት በተጨማሪ ለተማሪዎች የሚሰጥ ነው።

የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ወጣት አዋቂዎች ለከፍተኛ ትምህርትም ሆነ፣ ለሥራ ወይም ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎቶችን በተመለከተ ተገቢ መኖሪያ ለማግኘት የእርዳታ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው። ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ጊዜ ሰነዱ ውስጥ ያለው መረጃ በጣም ይጠቅማቸዋል። ሰነዱ የሚዘጋጀው ኢንተርኔት ላይ ያለ ፕሮግራምን በመጠቀም ነው። ሰነዱ የሚዘጋጀው በትምህርት ቤት ሠራተኛ እና በተማሪው፣ ከተማሪው ቤተሰብ ሓሳብ በመቀበል ነው።

የሰነዱ መረጃ የሚሰበሰበው የሽግግር ዕቅድ ማውጣት በሚከሰትበት በተማሪው የIEP ቡድን ስብሰባዎች ላይ መሆን አለበት። የሽግግር ዕቅድ ሲወጣ ሰነዱ እንደ መምሪያ ሊጠቅም ይችላል። ሰነዱ ስለ ወጣቱ ችሎታዎች፣ ጠንካራ ጎኖች እና ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉትን/ጓትን ድጋፎች ጠቃሚ መረጃ የያዘ ሲሆን ለወደፊት ቀጣሪዎች፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች እና የአዋቂ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃ ይሰጣል።

የሜሪላንድ መውጫ ሰነድ ውስጥ አሥር ክፍሎች አሉ። ከዚህ በታች የተጠቀሱት እያንዳንዱ ክፍሎች ስለ ወጣት አዋቂው በይበልጥ ዝርዝርና ልዩ መረጃ የያዙ ናቸው።

- የግል መረጃ
- የትምህርት ዘርፍ

- *ለትምህርት አስፈላጊ ሁኔታዎች/ድጋፎች*
- *የሥራ ምርጫዎች*
- *የግል ባሕርዮች*
- *የግል ፍላጎቶች*
- *ለሥራ አስፈላጊ ሁኔታዎች/ድጋፎች*
- *የመደበኛ ችሎታዎች ማርኮች*
- *የሥራ ታሪክ*
- *የምስክር ቃሎች/ደብዳቤዎች*

# *መብትና ብቃት ሲነጻጸሩ*

*በብቃት ላይ የተመሠረተ የመንግሥት ትምህርት እና የአዋቂ አገልግሎቶች የማግኘት መብት ግራ ሊያጋባ ይችላል። በሜሪላንድ ውስጥ፣ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች እያገኘ ያለ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ዕድሜው* 21 *ዓመት እስከሚሞላበት* (IDEA 2004) *ሙሉ የትምርህት ዘመን ድረስ ወይም የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ የመርሃ ግብር ፍጻሜ የምስክር ወረቀት የሚያስገኙትን መስፈርቶች ካሟላ ተገቢ ነጻ የመንግሥት ትምህርት የማግኘት መብት አለው። ተማሪው አንድ ጊዜ ከትምህርት ቤት ከወጣ/ከወጣች በኋላ፣ ከአዋቂ አገልግሎት ድርጅቶች አገልግሎት ለማግኘት ገንዘብ ካለ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላት* <u>*አለበት/አለባት*</u>*። እና የገንዘብ*

# *የሜሪላንድ አዋቂዎች አገልግሎት ድርጅቶች*

*የሚከተለው ክፍል ልጅዎ ትምህርት ቤት ከለቀቀ/ከለቀቀች በኋላ* <u>*ምናልባት*</u> *አገልግሎቶች ሊሰጡ የሚችሉ ወይም አገልግሎቶች ሊገዙ የሚችሉ ድርጅቶችን በዝርዝር ይናገራል። ልጅዎ በተቻለ መጠን እራሱን/እራሷን እንዲችል/እንድትችል የሚያደርጉ አገልግሎቶች የሚሰጡ አራት የስቴት ድርጅቶች አሉ። ልጅዎ ከማንኛቸውም ከነዚህ ድርጅቶች አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ሆኖ ለመገኘት ልዩ የሆኑ መስፈርቶች ማሟላት አለበት። ልዩ የብቃት መስፈርቶች የድርጅት ገለጻ ውስጥ ተብራርተው ይገኛሉ። አራቱ ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው፡*

1. *የሜሪላንድ እድገት ነክ የአካል ጉዳት አስተዳደር* (Maryland Developmental Disabilities Administration)
2. *የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል/የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ* (Division of Rehabilitation Services/Maryland State Department of Education)
3. *የአእምሮ ጤንነት አስተዳደር/የጤናና የአእምሮ ደህንነት መምሪያ* (Mental Hygiene Administration/Department of Health and Mental Hygiene)

4. *የሰው ኃይል ዝግጅት እና የአዋቂ ትምህርት/የሚሪላንድ የሰው ኃይል ፈቃድና ድንብ መምሪያ*

*ይህ ክፍል ልጅዎ ትምህርቱን/ትምህርቷን በከፍተኛ ደርጃ ት/ቤት፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ ኮሌጆችን፥ ኮምዩኒቲ ኮሌጆችን ወይም የሙያ ስልጠና ት/ቤቶችን ጨምሮ፣ በሚከታተልበት/በምትከታተልበት ጊዜ ማመልከቻ ማስገባት የሚችልባቸውን የከፍተኛ ደረጃ የአካል ጉዳት ድጋፍ አገልግልግሎቶችን በዝርዝር ያብራራል።*

## *1. የሚሪላንድ እድገት ነክ አካል ጉዳት አስተዳደር (DDA)*

*የእድገት ነክ አካል ጉዳት አስተዳደር፣ በሚሪላንድ የጤናና የአእምሮ ደህንነት መምሪያ ድጋፍ አማካኝነት የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል የሚያስችሏቸው አገልግሎቶች እንዲያገኙ የተቀናጀ የአገልግሎት መስጫ ሥርዓት ያቀርባል። አገልግሎቶች የሚሰጡት ያለ ትርፍ በሚሠሩ በኩል በሚሰጡ በተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎቶች በኩል ነው።*

*የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦቻቸው ማደግ እንዲችሉ የሚያስችሏቸውን ነገሮች ማግኘት እንዲችሉ፣ አጠቃላይ ሕዝቡ የሚያገኘውን ነገር ጨምሮ፣* DDA *ከቤተሰቦች፣ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ የክልልና የስቴት ድርጅቶች እና ተሟጋቾች ጋር ሽርክናና እምነት ለመፍጠር መሪ ሚና ይጫወታል። አንድ ግለሰብ መብቶችና ክብር ይገባዋል ብለን ስለምናምን የሚከተሉትን ለማድረግ ቃል እንገባለን፦*

- *እድገት ነክ አካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦቻቸው ለነሱ የሚያስፈልጋቸውን ዓይነት አገልግሎቶችና ድጋፎች እንዲያገኙ ኃይል መስጠት።*
- *የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ከማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ማህበራዊ ኑሮ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።*
- *ደንበኛ የተደሰተባቸውና ጥራት ያላቸው፣ የግል እድገትና መዳበርን የሚያበረታቱ ዳጋፎች።*
- *የሚሪላንድ ዜጋዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የመደቧቸውን ነገሮች መጠቀም የሚያስችል፣ የገንዘብ ኃላፊነት የወሰደና አመቺ የሆነ የአገልግሎት ሥርዓት ማቋቋም።*

*የ*DDA *ዓላማ ኃላፊነቱን ወስዶ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው በሁሉም ዓይነት የማህበረሰብ ኑሮ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ። በተጨማሪም የ*DDA *ዓላማ በቂ ኃይል ሰጥቷቸው ለእድገት፣ ራስን ለመቻልና ውጤታማ ለመሆን አስፈላጊውን ድጋፍና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ነው።* DDA *የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የራሰን ዕድል በራስ መወሰን የሚያስቹልትን አራቱን ነጥቦች ማድረግ እንዲችሉ ነው፦* (1) *የምርጫ ነጻነት፣* (2)*የአገልግሎቶች እና የድጋፍ ስልጣን፣* (3)*ያሉትን ምንጮች የማዘጋጀት ኃላፊነት፣ እና* (4)*ማህበረሰብ ውስጥ ለመኖር የሚያስፈልጉት ድጋፎች።*

**ብቃት**

*አንድ ግለሰብ የሚከተሉት ዓይነት ከባድ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ካለበት የተጧሉ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት አለው፦*

- *በሐኪም ምርመራ ከተደረሰበት የአእምሮ ሕመም ውጪ የሆነ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ወይም የተቀላቀለ የአእምሮና የአካል ጉዳት፣*

- *ዕድሜው* 22 *ዓመት ከመሆኑ በፊት የተከሰተ ከሆነ፣*
- *ሁልጊዜም የመቀጠል ዕድሉ ከፍተኛ ከሆነ*
- *ከውጭ እርዳታ ሳያገኝ ወይም ቀጣይ እና መደበኛ እርዳታ ሳያገኝ ራሱን ችሎ መኖር የማይችል ከሆነ፣*
- *ልዩ፣ ብዙ ዓይነት ወይም መደበኛ ጥንቃቄ፣ ሕክምና ወይም ለዛ ግለሰብ የተዘጋጁ ሌሎች አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ ከታየ።* (Health General 7-101[e])

*አንድ ግለሰብ የድጋፍ አገልግሎቶች ብቻ ለማግኘት ብቁ የሚሆነው እርሱ ወይም እርሷ የሚከተሉትን ዓይነት ከባድና ቀጣይ ጉዳት ሲኖርበት/ሲኖርባት ነው፦*

*ሀ. በሐኪም ምርመራ ከተደረሰበት የአእምሮ ሕመም ውጪ የሆነ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ወይም የተቀላቀለ የአእምሮና የአካል ጉዳት፣*

*ለ. ሁልጊዜም የመቀጠል ዕድሉ ከፍተኛ ከሆነ (Health General 7-403[c])*

*ግለሰቦች የ* DDA *አገልግሎቶች ለማግኘት ማመልከቻ አስገብተው ብቃት እንዳላቸው መወሰን አለበት። አንድ ግለሰብ የ* DDA *አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ ነው ተብሎ ከተወሰነ ከሚከተሉት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ጋር ይመደባል። እነዚህም የተደረደሩት አመልካቾች አገልግሎት በሚያገኙበት ቅደም ተከተል ነው፦*

- *ዘርፍ* I - *ችግር መፍታት*
- *ዘርፍ* II - *ችግር መከላከያ*
- *ዘርፍ* III - *ያሁኑ ጥያቄ*

DDA ***የሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦***

- ***የቤትና የማህበረሰብ አገልግሎቶች መብት አሳልፎ መስጫ (Home and Community-Based Services Waiver)፦*** *የሜዲኬድ ቤትና የማህበረሰብ አገልግሎቶች* (HCBS) *መብት አሳልፎ መስጫ መርሃ ግብር በሶሻል ሴክዩሪቲ ሕግ አንቀስ ቁጥር* §1915(c) *ውስጥ የተፈቀደ ነው። የሜዲኬድ ተጠቃሚዎች ማህበረሰብ ውስጥ እንዲኖሩና ተቋማት ውስጥ መኖር እንዳይኖርባቸው ስቴቱ የተለያዩ የቤትና የማህበረሰብ አገልግሎቶች እንዲያቀርብ መርሃ ግብሩ ይፈቅዳል። መብት አሳልፎ መስጫው የሚመለከታቸው ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ ስቴቱ የራሱን መብት አሳልፎ መስጫ የማዘጋጀት ነጻነት አለው። የመብት አሳልፎ መስጫ አገልግሎቶች ከሜዲኬድ ስቴት ፕላን፣ ከፌዴራል፣ ከስቴትና ከክልል መንግሥት መርሃ ግብሮች፣ እንዲሁም ከቤተሰቦችና ከማህበረሰቦች ከሚገኝ ድጋፍና አገልግሎቶች በተጨማሪ የሚገኙ ናቸው። ሙሉ ብቃት አላቸው ተብለው የተወሰነላቸው ግለሰቦች (ለድጋፍ አገልግሎቶች ብቻ ብቃት አላቸው የተባሉ ሳይሆኑ)፣ የጤናና የአእምሮ ደህንነት መምሪያ የመብት አሳልፎ መስጫ ብቃት ክፍል የሜዲኬድ ብቃት አላቸው ብሎ ያላቸው ሰዎች በዚህ መብት አሳልፎ መስጫ ሥር ብቃት አላቸው።*

- ***የአዲስ አስተዳደሮች መብት አሳልፎ መስጫ* (New Directions Waiver)፦** *አዲሱ የአስተዳደር መብት አሳልፎ መስጫ ግለሰቦች የገንዘብ አስተዳደር አገልግሎት* (FMS) *እና የደላላ ድጋፍ በመጠቀም የራሳቸውን የተወሰኑ አገልግሎቶች እንዲያስተዳድሩ ይፈቅዳል። የድለላ ድጋፍ ሰጪው ግለሰቡ የራሱን አገልግሎቶች እንዲያስተዳድር እርዳታ ያቀርባል፣ ግለሰቡም የራሱን አገልግሎቶች ለማስተዳደር የሚያስፈልጉትን ችሎታዎች እንዲያገኝ ይረዳል። የደላላ ድጋፍ ከአገልግሎቶች ማስተባበር ጋር አብሮ የሚሄድ ነው ምክንያቱም የአገልግሎቶች ማስተባበር አጠቃላይ ዕቅድ ማውጣት፣ ወደ ሌላ የመምራትና የጥራት ማረጋገጫ ሥራ የሚሠራ ሲሆን የደላላ ድጋፍ ደግሞ የዕለትተለት መርሃ ግብር አስተዳደርን ይከታተላል። በአዲስ አስተዳደሮች በኩል የሚገኙ አገልግሎቶች ግለሰቦች እራሳቸው ቤት ውስጥ ወይም ቤተሰቦቻቸው ቤት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ለመኖር የሚያስችሏቸው ዓይነት አገልግሎቶች ናቸው። ለተጠቃሚ የተዘጋጁ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፦ ማገገሚያ፣ ድጋፍ ያለበት ሥራ፣ ሥራ ማግኛና ለራስ እንዲሆን ማመቻቻ አገልግሎቶች፣ የማህበረሰብ ትምህርት አገልግሎቶች፣ በማህበረሰብ የተደገፈ መኖሪያ፣ መጓጓዣ፣ አካባቢው ውስጥ መንቀሳቀስ መቻል፣ የቤተሰብና የግል ድጋፍ አገልግሎቶች፣ የሽግግር አገልግሎቶች፣ የደላላ ድጋፍ፣ ረዳት ቴክኖሎጂና መሣሪያ።*

- ***የማህበረሰብ መንገዶች* (Community Pathways)፦** *የማህበረሰብ መንገዶች መብት አሳልፎ መስጫ እድገት ነክ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ቤታቸውና ማህበረሰቡ መካከል መኖር እንዲቀጥሉና በግድ አንድ ተቋም ውስጥ መኖር እንዳይኖርባቸው ድጋፍ ይሰጣል። በዚህ መብት አሳልፎ መስጫ ሥር የሚሰጡ አገልግሎቶች "ባህላዊ" አገልግሎቶች ሲሆኑ፣ ለግለሰቦች የሚውለው የአገልግሎት ገንዘብ ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የተሰጠ ነው። አገልግሎቶቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦ የኑሮ እርዳታ እና የተራዘመ የኑሮ እርዳታ (ድጋፍ ያለው ሥራን፣ ሥራ ማግኛና ለራስ እንዲሆን ማመቻቻ አገልግሎቶች፣ እና የማህበረሰብ ትምህርት)፣ በማህበረሰብ ድጋፍ የሚኪያሄድ መኖሪያ፣ በማህበረሰብ ድጋፍ የሚሆን የኑሮ ሁኔታ፣ ማገገሚያ፣ የመጠቀሚያ ቦታዎች ማስተባበር (የጉዳይ አስተዳደር)፣ የአካባቢ ማሻሻሎች፣ የቤተሰብና የግለሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች፣ የሽግግር አገልግሎቶች፣ የሐኪም ቀጠሮ ሲኖር ልጅ መጠበቅ፣ እና ረዳት ቴክኖሎጂና መሣሪያ።*

- ***መጀመሪያ ሥራ* (Employment First)፦** *የ*DDA *አገልግሎቶች የተቋቋሙት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ሁሉ ዕድሉ፣ ስልጠናው እና ከጠንካራ ጎናቸው ጋር አብሮ የሚሄዱ ድጋፎች ከተሰጧቸው መሥራት ይችላሉ በሚል እምነት ላይ ነው። አገልግሎቶች የሚሰጡት በተቀነባበረ አካባቢ ውስጥ ሲሆን፣ ከግለሰቡ የግል ዕቅድ ጋር አብረው እንዲሄዱ ሆነው ይቀርባሉ፤ የሚዘጋጁትም በግለሰብ ላይ በተመሠረተ የዕቅድ ሂደት ሲሆን ይህም በተቀነባበረ አካባቢ ውስጥ እና ማህበረሰብ ውስጥ ለመቀላቀል ሊያጋጥሙ የሚችሉትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ዕቅዶች ወጥተው ነው።*

  ***ማሳሰቢያ፦** የDDA አገልግሎቶች ለሚያገኙና ሥራ ለመሥራት ዕድሜያቸው የሚፈቅድ ሰዎች (ከ16 ዓመት እስከ 64 ዓመት) ሥራ መሥራት የ"መጀመሪያ" አማራጭ ይሆናል።*

- ***የአገረ-ገዥ ተሸጋጋሪ ወጣት እርምጃ* (Governor's Transitioning Youth Initiative):-** *የአገረ-ገዢው የሽግግር ወጣቶች እርምጃ* (GTYI) *በ1989 ዓ.ም. የተዘጋጀው ከባድ ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ቤት ከጨረሱ በኋላ ሥራ ሠረተው ለሜሪላንድ የወደፊት ጊዜ አስተዋጾ ማድረግ እንደሚችሉ ለማስመስከር ነው።። የሽግግር ወጣቶች ለብቃትና አገልግሎቶች በቅድሚያ ለማግኘት ልዩ የብቃት ረድፍ ውስጥ ነው። በአገረ-ገዢው የሽግግር ወጣቶች እርምጃ በኩል፣* DDA *ከማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል* (DORS) *ጋር በመተባበር፣ ብቃት ላላቸው የተመረቁ*

ተማሪዎች ድጋፍ ያለው ሥራ ማግኘት ችሏል። እነዚህ ተማሪዎች በሌላ በኩል ቢሆን ኖሮ የ DDA አገልግሎቶች ማግኘት አይችሉም ነበር። አንድ ግለሰብ የአገረ-ገዢው የሽግግር ወጣቶች አርምጃ (GTYI) ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ለመሆን ሙሉ በሙሉ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት መሆን አለበት። በተጨማሪም ተማሪው ብቃት የሚኖረው ከ21ኛ ዓመት ልደቱ እስከ 22ኛ ዓመት ልደቱ ድረስ ነው። የምረቃ ቀኑ ከ21ኛ ዓመት ልደቱ በኋላ ከሆነ፣ ግለሰቡ ከተመረቀበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ብቁ ሆኖ ይቆያል።

በ GTYI በኩል የሚገኙ አገልግሎቶች ሥራ ለማግኘት በተከታታይ ይሚጠቀሟቸው ዓይነት አገልግሎቶች አይደሉም። አገልግሎቶች በዝርዝር የተጻፉት በጣም ከተቀነባበረው ጀምሮ ነው።

- ***ድጋፍ ያላቸው የሥራ አገልግሎቶች (Supported Employment Services)*** አንድ ሰው ሥራ አግኝቶ ማቆየት እንዲችል ወይም ማህበረሰብ ውስጥ የራሱን ንግድ ማቋቋም እንዲችል የሚረዱ በማህበረሰቡ ላይ የተመሠረቱ አገልግሎቶች ናቸው። ድጋፎቹ አብዛኛውን ጊዜ የሥራ አፈላለግ ረዳቶች ሲሆኑ፣ የድጋፎቹ ብዛት ግለሰቡ እንደሚያስፈልገው ዓይነት ይለያያሉ። ድጋፎቹ ቀጣይ ሊሆኑ ወይም ከጊዜ በኋላ ሊያቆሙ ይችላሉ። ለምሳሌ የራስ ንግድ፣ በራስ ሥራ እና በቡድን ሥራ (አነስተኛ ወይም ተንቀሳቃሽ ሠራተኞች)። ይህ አገልግሎት በአዲስ አስተዳደሮች ሙብት አሳልፎ መስጫ (New Directions Waiver) ሥር በራስ ማስተዳደር ይቻላል።

- ***ሥራ ማግኘትና ለራስ እንዲስማማ ማመቻቻ አገልግሎቶች (Employment Discovery and Customization Services)*** ለተወሰነ ጊዜ የሚቆዩ በማህበረሰብ ላይ የተመሠረቱ አገልግሎቶች ሲሆኑ (የ3 ወር ቆይታ ያላቸው) አንድ ሰው ተወዳድሮ ሥራ እንዲያገኝ ተመጣጣኝ ደመወዝ እንዲከፈለው ስልጠና፣ ማመቻቻና ማግኛ የሚያቀርቡ አገልግሎቶች ናቸው። አገልግሎቶቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦ በማህበረሰብ የተመሠረተ የሁኔታ ግምገማ፣ ሥራ ማጎልበት፣ የሥራ ትንተና እንቅስቃሴዎች፣ የሥራ ላይ ስልጠና፣ የሥራ ችሎታ ስልጠና፣ የሥራ ዕቃዎች፣ ሥርዓቶች እና መመሪያዎች ማስተካከል፣ ወዘተ። ይህ አገልግሎት በአዲስ አስተዳደሮች ሙብት አሳልፎ መስጫ (New Directions Waiver) ሥር በራስ ማስተዳደር ይቻላል።

- ***የማህበረሰብ ትምህርት አገልግሎቶች (Community Learning Services)*** በማህበረሰቡ ላይ የተመሠረቱ፣ ሰዎች ሥራ ለማግኘት አስፈላጊዎቹን ችሎታዎች እና የማህበረሰብ ድጋፎች እንዲያዳብሩ የሚረዱ አገልግሎቶች ሲሆኑ፣ በተጨማሪም እድገት የሚያበረታቱ፣ እንቅስቃሴዎች የሚያቀርቡ፣ ልዩ እርዳታ፣ ድጋፍና ትምህርት የሚሰጡ ናቸው። አገልግሎቶች በከፍተኛ ደረጃ ለግለሰቡ የተዘጋጁ ሲሆኑ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦ በራስ የመወሰን/ለራስ የመቆም ስልጠና፣ ወርክሾፖችና ክፍሎች ጋር ለመሄድ ድጋፍ፣ እርስ በርስ መማር፣ የፈቃደኛ ሥራዎች፣ ጤንነትን፣ ማህበራዊ ኑሮን የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎች ወዘተ። ይህ አገልግሎት በአዲስ አስተዳደሮች ሙብት አሳልፎ መስጫ (New Directions Waiver) ሥር በራስ ማስተዳደር ይቻላል።

- ***ባህላዊ የዕለት ኑሮ (Traditional Day Habilitation)*** በአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች ሲሆኑ፣ የተዘጋጁትም የእንቅስቃሴ፣ የንግግር፣ ራስን የመጠበቅ እና የመዝናኛ ችሎታዎችና ከማህበረሰብ ጋር ተቀላቅሎ የመኖር እንቅስቃሴዎችን ለማበረታታት ነው።

- ***የሥራ መግቢያ ቲኬት መርሃ ግብር* (Ticket to Work Program)**፦ *የሥራ መግቢያ ቴኬት መርሃ ግብረ እና ራስን የመቻል መርሃ ግብር ሥራ የመሥራት ፍላጎት ላላቸው የአካል ጉዳት*

**ያለባቸው ሰዎች የተዘጋጀ መርሃ ግብር ነው። በሥራ መግቢያ ቲኬት መርሃ ግብር ሥር፣ የሶሻል ሴክዩሪቲ አስተዳደር አካል ጉዳት ላለባቸው ተጠቃሚዎች ስኬታማ ሥራ መሥራት እንዲችሉ አገልግሎቶችና ድጋፎች ማግኛ ቲኬት ይሰጣል።**

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም አገልግሎቶች ለማግኘት ማመልከቻ ለማስገባት፦**
www.ddmaryland.org
1-877-468-3464

**የሶሻል ሴክዩሪቲ አስተዳደር ድጋፍ ያለው ሥራ እርዳታ፦**
www.socialsecurity.gov/work/
1-800-772-1213

**የሥራ ቲኬት መርሃ ግብር፦**
www.yourtickettowork.com/

## 2. የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል (DORS)

*የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ፣ የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል፣ በሜሪላንድ ውስጥ ሙያ ነክ ማገገሚያ መርሃ ግብር ያስተዳድራል፤ ይህም ከባድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ሥራ እንዲያገኙና ራሳቸውን እንዲችሉ የሚረዳ ነው። መምሪያው ቅድሚያ የሚሰጠው ከባድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወደ ሥራ ዓለም፣ ወደ ከፍተኛ ትምህርት እና/ወይም ወደ ሙያ ስልጠና ሲሸጋገሩ የሚረዷቸው ጠቃሚ መርሃ ግብሮችና አገልግሎቶች ማቅረብ ላይ ሲሆን፣ ከትምህርት ቤት ሥርዓቶች ጋር፣ የአካል ጉዳት ካለባቸው ተማሪዎች ጋር፣ ከማህበረሰብ መርሃ ግብሮችና ከቤተሰቦች ጋር ያለውን ሽርክና በአክብሮት ይይዛል።* DORS *የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች አገልግሎቶችን ለመግለጽና አቅርቦቱን ለማቃለል ከእያንዳንዱ የሜሪላንድ ክልል የትምህርት ቤት አውራጃዎች ጋር ስምምነቶች አሉት።*

DORS *መርሃ ግብሮችና አገልግሎቶች የሚሰጠው በመስክ አገልግሎቶች ቢሮ* (Office of Field Services)፣ *በአይነስውራንና ማየ አገልግሎቶች* (Office for Blindness & Vision Services) *እና በሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ ማዕከል* (Workforce & Technology Center) *በኩል ነው።*

- ***የDORS ሠራተኞች፦*** *የአካል ጉዳት ካለባቸው ጋር በተለይ የሚሰሩ መካሪ የማገገሚያ ባለሙያዎች በሜሪላንድ ውስጥ በየቦታው በ* DORS *ቢሮዎች ውስጥ ይገኛሉ። የ*DORS *ሽግግር መካሪዎች በእያንዳንዱ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመድበው፣ ከትምህርት ቤቱ ሠራተኞችና ከሽግግር አስተባባሪው እንዲሁም ከልዩ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች ጋር የቅርብ ሥራ ግንኙነት የፈጠሩ ናቸው። የ*DORS *ሠራተኞች ለተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው በሽግግር ዝግጅቶችና ሌሎች ተገቢ የትምህርት ቤት በዓሎች ላይ ስለ ሽግግር መረጃ ይሰጣሉ። ባብዛኛው የሽግግር መካሪው በቀጥታ ከባድ የአካል ጉዳት ካላቸው ተማሪዎች ጋር አብሮ መሥራት የሚጀምረው ት/ቤት ሊጨርሱ አንድ ዓመት ሲቀራቸው መጀመሪያው ላይ ነው። ብቃትንና መቅደም ያለባቸውን አገልግሎቶች ለመገምገም እንደተገቢነቱ ከተማሪውና ከቤተሰቡ ጋር አብረው ይሠሩና ከዛ በመቀጠል ተማሪው በት/ቤት እንዳለ ከዛም ት/ቤት ከጨረሰ በኋላ የሚቀርቡ የሥራ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ዕቅድ ያወጣሉ።*

- ***የብቃት እና በቅድሚያ የሚሰጡ አገልግሎቶች (Eligibility and Priority of Services)፦*** *በፌዴራል ሕግ መሠረት ግለሰቦች ለ* DORS *የሙያ እድሳት መርሃ ግብር* (DORS Vocational Rehabilitation (VR)) *ብቁ የሚሆኑት ይሚከተሉትን ካሟሉ ነው፦ (1) ሥራ ለማግኘት በከባዱ እንቅፋት ሊሆን የሚችል ዓይነት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ካላቸው፣ (2) አገልግሎቶቹ በሥራ ውጤት ረገድ የሚረዷቸው ከሆነ እና (3) ሥራ ለመሥራት ሙያ ነክ እድሳት አገልግሎቶች የሚያስፈልጓቸው ከሆነ። የሚሰጠው አገልግሎት የተወሰነ ስለሆነ* DORS *አገልግሎት የሚሰጠው "ከባድ" ወይም "በጣም ከባድ" የአካል ጉዳት ላላቸው ግለሰቦች ብቻ ነው። የዚህም ፍቺ ለረጅም ጊዜ ብዙ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸው እና ያለባቸው ጉዳት እንደ መንቀሳቀስ፣ መግባባት፣ ራስን መንከባከብ፣ ራስን ማስተዳደር፣ ማህበራዊ ችሎታዎች፣ ሥራ መቻል እና የሥራ ችሎታ የመሳሰሉ የመንቀሳቀስ ችሎታዎችን በከባዱ የሚያስቸግሩ ጉዳቶች ያለባቸው ግለሰቦች ናቸው። አገልግሎቶችን ለማግኘት ስምን አስመዝግቦ ወረፋ መጠበቅ ሊያስፈልግ ይችላል።*

- ***አገልግሎቶችን መጠቀም።*** *(1) በልዩ ትምህርት ውስጥ፣ (2) 504 ፕላኖች ውስጥ ወይም (3)ከባድ የጤና መቃወስ ያለባቸው ከባድና በጣም ከባድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የሚከተሉትን እስካሟሉ ድረስ መጠቀም አለባቸው፦*

1) የሥራ ዓላማ ካላቸው
2) ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቢያንስ በአንዱ ላይ ከባድ ችግር እንዳላቸው ካስመሰከሩ (*ብቃትና የቅድሚያ አገልግሎቶች* የሚለውን ይመልከቱ)

*ማሳሰቢያ፦* ተጨማሪ የሴክዩሪቲ ገቢ (SSI) ወይም የሶሻል ሴክዩሪቲ የጉዳት ዋስትና (SSDI) የሚያገኙ ተማሪዎች የ VR አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት እንዳላቸውና ከባድ የአካል ጉዳት እንዳላቸው ተብለው ይወሰዳሉ፣ እንዲሁም የሥራ ዓላማ ካላቸው መጠቀም አለባቸው።

ተማሪዎች የሚከተለው ሁኔታ የሚመለከታቸው ከሆነ መጠቀም የለባቸውም፦

- ከ DORS የሥራ አገልግሎቶች የማግኘት ፍላጎት የላቸውም
- ያለባቸው ጉዳት የሥራ ችሎታን *በከባዱ* የማያደናቅፍ ዓይነት ሆኖ አነስተኛ ከሆነና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት እና/ወይም ሥራ እንዳስፈላጊነቱ በመለስተኛ እርዳታዎች ማከናወን የሚችሉ ከሆነ።

- **የጊዜ ገደብ እና የመጠቀሚያ መንገዶች፦** ባብዛኛው በሽግግር ላይ ካሉ ተማሪዎች ጋር DORS አብሮ መሥራት የሚጀምረው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሊጨርሱ አንድ ዓመት ሲቀራቸው መጀመሪያው ላይ ነው። ከዛ አስቀድሞ መጀመር የሚያስፈልግበት ልዩ ምክንያት ካለ፣ ልዩ አስተያየት ሊደረግለት ይችላል። የተማሪዎች ጥቆማ የሚያስተባብሩት የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ከ DORS የሽግግር መካሪ ጋር አብሮ በመሥራት ነው። ከጥቆማው ጋር ትምህርት ቤቱ አብሮ የሚሰጠው መረጃ (ለምሳሌ የመረጃ ግምገማ፣ የመውጫ ሰነድ፣ የግል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ወይም ፕላን 504) ብቃትን ለመወሰንና የግል ሥራ ዕቅድን ለማውጣት ይጠቅማል።

- **ሥራ ለማግኘት የግል ዕቅድ (Individualized Plan for Employment (IPE))፦** The የDORS አማካሪ *ሥራ ለማግኘት የግል ዕቅድ* (IPE) የሚባል ብቃት ያላቸው ግለሰቦች የአገልግሎቶች ዕቅድ እንዲያወጡ አብሯቸው ይሠራል። IPE ውስጥ የሚጠቃለሉት አገልግሎቶች አንድ ተማሪ ከቤተሰቡ ጋር አብሮ በመሥራት የግል የሥራ ዓላማ ለማውጣት የሚያስፈልጉት ናቸው። የሥራ ዓላማውና አስፈላጊዎቹ አገልግሎቶች በተማሪው የግል ጠንካራ ጎን፣ ማግኘት በሚችላቸው ጥቅሞች፣ ፍላጎቶች፣ አስፈላጊ ነገሮች እና አውቆ በሚመርጣቸው ነገሮች የተመሠረቱ ናቸው። IPEው የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦ (1) የሥራ ዓላማ፣ (2) ሥራ ለማግኘት የጊዜ ገደብ ማውጣት፣ (3) የሚያስፈልጉት አገልግሎቶች፣ (4) ለአገልግሎቶች ማን እንደሚከፍል፣ (5) አገልግሎቶች ስኬታማ መሆናቸው እንዴት እንደሚወሰን። ልዩ ትምህርት ለሚያገኙ ተማሪዎች፣ IPEው የሚዘጋጀው ከግል ትምህርት ዕቅድ ጋር አብሮ እንዲሄድ ተደርጎ ነው። አገልግሎቶቹ ከመጀመራቸው በፊት IPEው በ DORS መጽደቅ አለበት።

- **የማገገሚያ አገልግሎቶች፦** ተጠቃሚው በሚያስፈልጉት ነገሮች መሠረት DORS ብዙ የተለያዩ ዓይነት አገልግሎቶች ማቅረብ ወይም ማስገኘት ይችላል። እነዚህም የሙያ ግምገማ፣ የሙያ ምርጫ፣ ምክርና ጥቆማ፣ ረዳት ቴክኖሎጂ፣ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት (የሙያ ስልጠና፣ ኮምዩኒቲ ኮሌጅ፣ ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ) እና የሥራ ምደባ አገልግሎቶች። አገልግሎቶች የሚቀርቡት በDORS መካሪዎች፣ በጸደቁ የማህበረሰብ አገልግሎት አቅራቢዎች ሲሆን የሚሰጡትም በስሜን ምስራቅ ባልቲሞር በሚገኘው የመምሪያው የተቀነባበረ ማገገሚያ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ ማዕከል (Workforce & Technology Center) ውስጥ ነው።

- ***የአገልግሎቶች ክፍያ፦*** DORS ***የሚከፍለው የ*** DORS ***ባለስልጣን አስቀድሞ ለፈቀዳቸውና በጽሑፍ ላጸደቃቸው አገልግሎቶች ብቻ ነው። መምሪያው የእያንዳንዱን ቤተሰብ ገቢ አይቶ ለአገልግሎቶች ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያድረጉ የሚያስችል መንገድ አለው።*** SSI ***የሚያገኙ ግለሰቦች ለአገልግሎቶች እንዲከፍሉ አይጠበቅባቸውም። የ***DORS ***ተጠቃሚዎች ለተወሰኑ አገልግሎቶች ወጪ እንዲያደርጉ አይጠበቅባቸውም፣ ለምሳሌ ለግምገማ፣ ለምክር/መምራት/ጥቆማ፣ ለሥራ ምደባ አገልግሎቶች፣ ድጋፍ ያለው ሥራ፣ የሙያ ማሻሻያ አገልግሎቶች ውስጥ የመሳተፍ ግዴታ ሲኖር የመግባቢያ እርዳታዎች መሣሪያዎችና አገልግሎቶች፣ እና የግል እርዳታ አገልግሎቶች።***

- ***ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት፦*** በ IPEው ***ውስጥ ያለውን የጸደቀውን የሥራ ዓላማ ለማሟላት ስልጠና አስፈላጊ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ወጪዎችን ለመሸፈን*** DORS ***እርዳታ ሊያደርግ ይችላል።*** DORS ***የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ዋና የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ አይደለም።*** IPEው ***ውስጥ ያለ የጸደቀ የሥራ ዓላማ ለማሳካት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ተጠቃሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በየዓመቱ ለትምህርት ገንዘብ ስጦታዎችና ስኮላርሺፖች ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው።*** IPEው ***ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የተጠቀሰ ከሆነ፣ የ***4 ***ዓመት ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳጋፍ ለመስጠት ልዩ አስተያየት ካልተደረገ በስተቀር ኮምዩኒቲ ኮሌጅ ውስጥ እስከ*** 60 ***ክሬዲቶች*** DORS ***ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል።***

***በይበልጥ መረጃ ለማግኘት የ*** DORS ***ድህረ ገጽን*** www.dors.state.md.us ***ይጎብኙ ወይም የ*** www.dors.state.md.us ***ሽግግር ባለሙያ ጋር በስልክ ቁጥር*** 410-554-9109፣ ***በነጻ ስልክ ቁጥር*** 888-554-0334፣ ***ወይም በኢሜል*** dors@dors.state.md.us ***ይገናኙ።***

***በይበልጥ መረጃ ለማግኘት፦***
www.dors.state.md.us
***ስልክ፦*** 410-554-9109
***የነጻ ስልክ፦*** 1-888-554-0334
***ኢሜል፦*** dors@dors.state.md.us

## *3. DHMH የአእምሮ ጤንነት አስተዳደር*

***የአእምሮ ጤንነት አስተዳደር*** (MHA) ***ከመንግሥት አእምሮ ጤንነት ሥርዓት*** (PMHS) ***በላይ ስልጣን አለው፣ ይህም የሚያካትተው የአገልግሎት አቅርቦት፣ የፖሊሲ ማዳበር፣ ስቴቱ በሙሉ ውስጥ ዕቅድ ማውጣት፣ የጥቅም ማግኛ ምደባ እና ቀጣይ የጥራት ማሻሻያ ኃላፊነቶች። ሜዲኬድ ለማግኘት ብቃት ላላቸውና የአእምሮ ሕመማቸው ከፍተኛ ስለሆነና ገንዘብ በቂ ስለሌላቸው በመንግሥት የተደገፉ አገልግሎቶች ለሚያገኙ ሰዎች*** MHA ***የማህበረሰብ የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። ባብዛኛው እነዚህ አገልግሎቶች የሚቀርቡት በየአገልግሎቱ የሚከፈል ክፍያ*** (FFS) ***ሥርዓት ነው። ለምሳሌ እንደ ባልደረባ ድጋፍ፣ የቤተሰብ ትምህርትና ስልጠና፣ እና ሌሎች ልዩ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ያሉ በ***FFS ***በኩል የክፍያ ካሳ የሌላቸው አገልግሎቶች እና ድጋፎች፣ ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ከክልሉ የአእምሮ ጤና ባለስልጣን ጋር ወይም ከዋና አገልግሎት ድርጅት*** (CSA) ***ሥር ኮንትራት ካላቸው አገልግሎት ሰጪዎች ሊገኙ ይችላሉ።***

***ሁሉን የሚያካትቱ የተለያዩ የመንግሥትና የግል አገልግሎቶች ይኖራሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ግለሰቦች በተቻላቸው መጠን ማህበረሰብ ውስጥ ተቀላቅለው እንዲሳተፉ ይረዳሉ።***

የአእምሮ ጤንነት አስተዳደር ዓላማ የተቀነባበረ፣ ሁሉን የሚያካትት፣ በቀላል ማግኘት የሚቻል፣ ለግል ብሔር የሚስማማ፣ ለዕድሜ የተመጣጠነ የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ ያለው የአገልግሎቶች ሥርዓት መፍጠር ሲሆን እነዚህም አገልግሎቶች የሚደግፉት የስነ አእምሮ ሕመም ያላቸውን ግለሰቦች ሆኖ ከባለቤቶች ጋር አብሮ ሆኖ ደህንነትን፣ ጤናንና መሻሻልን የሚያመጣ ሕክምናና ማገገሚያ ማቅረብ ነው።

**የዋና አገልግሎት ድርጅቶች (CSAs)** በክልል ደረጃ የመንግሥት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ዕቅድ የማውጣት፣ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸው የክልሉ የአእምሮ ጤንነት ባለስልጣኖች ናቸው። CSAዎች በጤናና በአእምሮ ደህንነት መምሪያ ስልጣን ሥር ያሉ ሲሆን የድርጅቱን አሰራር የሚያጸድቀው የአውራጃ አስተዳደር ተወካዮች ናቸው። CSAዎች በስቴቱ አውራጃዎች ውስጥ በሙሉ የሚሠሩ ሲሆን፣ አንዱ CSA ብዙ አውራጃዎችን ያጠቃልላል። እሱም የያዘው ሚድ ሾር ውስጥ ያሉ አምስት አውራጃዎችን ነው። አንዱ CSA ደግሞ ሎወር ሾር ውስጥ ያሉ ሁለት አውራጃዎችን የያዘ ነው። CSAዎች የግል፣ ያለትርፍ የሚሰሩ ድርጅቶች፣ የክልል አስተዳደር አካሎች ወይም ከፊል የመንግሥት አካሎች ሊሆኑ ይችላሉ።

**የአስተዳደር አገልግሎቶች ድርጅት (ASO),** በ MHA ሥር ባለው ኮንትራት መሠረት የአገልግሎቶች ፈቃድና የጥቅም አስተዳደር፣ የአስተዳደር መረጃ፣ የይግባኝ ሂደት እና የግምገማ አገልግሎቶች ይሰጣል።

## *የሜሪላንድ የመንግሥት የአእምሮ ጤንነት ሥርዓት (PMHS)፦*

**ብቃት**

የብቃት መስፈርት እንደ አገልግሎቱ ዓይነት ሊለያይ ይችላል። የመንግሥት የአእምሮ ጤንነት ሥርዓት ውስጥ ለመግባት መደበኛ የብቃት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- The individual has a mental health disorder, as defined in በDSM-IV-TR ፍቺ መሠረት ግለሰቡ የአእምሮ ጤና ሕመም አለበት እና
- ግለሰቡ ሜዲኬድ ያገኛል፣ ወይም
- ግለሰቡ ለሜዲኬድም ብቃት ኖሮት ግን በየአገልግሎቱ የሚከፈልበት ሥርዓት "የሁለቱም ብቃት" አለው ተብሎ ቆይቷል፣ ወይም
- ግለሰቡ ሜዲኬድ ለማግኘት ብቃት የሌለው ሲሆን በስነ አእምሮ ሕመምና በገንዘብ ችግር ምክንያት መንግሥት እና/ወይም የክልል ገንዘብ ለአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶች ይከፍልለታል።

ሜዲኬድ ያላቸው ሰዎች የPMHS አገልግሎቶች በሙሉ የማግኘት ብቃት አላቸው፣ ይህም የሚሆነው አገልግሎቱ በሕክምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

ሜዲኬድ ለማግኘት ብቃት የሌላቸው ሰዎች የስነ አእምሮ ምርመራ ተደርጎለት ሕክምና ያስፈልገዋል ከተባለ፣ የሜሪላንድ ነዋሪ ከሆነ እና ጥቅማጥቅም ለማግኘት ማመልከቻ ካስገባ፣ ለዛ አገልግሎት በሕክምና ያስፈልጋል የሚባሉትን መስፈርቶች ካሟላና ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን የሚያሟላ

ከሆነና ገንዘቡ እስካለ ድረስ ለአገልግሎቶች በሙሉ ብቃት አላቸው (ከሐኪም ቤት ተኝቶ መታከም፣ የድንገተኛ አገልግሎቶች ኣን ከፊል ሆስፒታል የመግባት አገልግሎቶች በስተቀር)፦

- ተጠቃሚው የገንዘብ ተረጂ ነው፣ CSAም አገልግሎት በአስቸኳይ ስለሚያስፈልግ ብቃት እንዲኖረው ፈቅዷል፣ ወይም
- ተጠቃሚው ባለፈው ሁለት ዓመታት ውስጥ የPMHS አገልግሎቶች አግኝቷል፣ ወይም
- ተጠቃሚው በአእምሮ ጤንነት ምክንያቶች አሁን SSDI እያገኘ ነው፣ ወይም
- ተጠቃሚው በሜሪላንድ ውስጥ ቤት አልባ ነው፣ ወይም
- ተጠቃሚው ከወህኒ ቤት፣ ከእሥር ቤት ወይም ከጸባይ ማረሚያ የተፈታው ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ነው፣ ወይም
- ተጠቃሚው ከሜሪላንድ የስነ አእምሮ ሆስፒታል የተፈታው ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ነው፣ ወይም
- በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መልቀቂያ ትእዛዝ መሠረት ተጠቃሚው አገልግሎቶች እያገኘው ነው።

ሜዲኬድ ለማግኘት ብቃት የሌላቸው ሰዎች የአእምሮ ሕክምና አገልግሎቶች ለማግኘት አነስተኛ ክፍያ መክፈል ሊኖርባቸው ይችላል።

የመንግሥት የአእምሮ ሕክምና ሥርዓት የጥቅም ጥርቅም የሚከተሉትን አገልግሎቶች ያካትታል። አገልግሎቶች በሙሉ የሚሰጡት በዛ አገልግሎት ልክ የሚያስፈልግት የሕክምና መስፈርቶች ከተሟሉ ነው።

- **የስነ አእምሮ ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ ታካሚ፦** የስነ አእምሮ ሆስፒታል ውስጥ ታካሚ አገልግሎት ከባድ የስነ አእምሮ ችግር ለሚያሳዩ ተጠቃሚዎች ወይም ራሳቸውን ወይም ሌሎች ሰዎችን ሊጎዱ የሚችሉ ዓይነት ተጠቃሚዎች ጥልቀት ያለው የአእምሮ ሕክምና እንዲያገኙ የሚያድርግ አገልግሎት ነው። የሆስፒታል ውስጥ ሕክምናው የስነ አእምሮ እና የክሊኒክ ግምገማ፣ የመድሃኒት አሰጣጥና አስተዳደር፣ የግለሰብ እና የቤተሰብ ምክር፣ በቡድን የሚደረግ ቴራፒ፣ የሕክምናና የነርስ ቁጥጥርና እርዳታ፣ የስነ አእምሮ ትምህርት እና ከሕክምና በኋላ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን ሊያጠቃልል ይችላል።
- **በስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት በከፊል ሆስፒታል መግባት፦** በከፊል ሆስፒታል መግባት የተመላላሽ፣ የአጭር ጊዜ፣ ጥልቀት ያለው፣ የስነ አእምሮ ሕክምና አገልግሎት ሲሆን የአገልግሎቶቹ ጥልቀት ሆስፒታል የሚሰጡትን፣ የሕክምናና የነርስ ቁጥጥርና እርዳታን ጨምሮ ዓይነት ነው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ሜዲኬድ ለማግኘት ብቃት ላላቸው ልጆች፣ ወጣቶች እና አዋቂዎች የሚቀርብ ጥቅም ነው።
- **የመኖሪያ ቤት ሕክምና፦** የመኖሪያ ቤት ሕክምና የተለያዩ የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶችን ምርመራና ሕክምናን ይጨምራሉ፣ በቀን 24 ሰዓት ሙሉ የሚገኙ የድንገተኛ የአእምሮ ሕመም አገልግሎቶችን ጨምሮ ጥልቀት ያለው ሕክምናን የያዘ Wraparound የሚባል የሕክምና ዓይነት ለልጅ፣ ለወጣት ወይም ለቤተሰብ ይሰጣል። ወጣቱ የሚኖረው ከቤተሰብ ጋር፣ የልጆች ማሳደጊያ

ቤት ውስጥ፣ የልጆች ማሳደጊያ የሕክምና ቤት ውስጥ፣ በቡድን የሚኖርበት ቤት ውስጥ፣ በቡድን ቴራፒ የሚሰጥበት ቤት ውስጥ ወይም የራስ መኖሪያ ቤት ውስጥ ሊሆን ይችላል።

- ***ፋታ፦*** *የፋታ መስጫ አገልግሎቶች በተጠቃሚው መኖሪያ ቤት ውስጥ ወይም ፈቃድ ያገኘ የማህበረሰቡ ቦታ ላይ ለአጭር ጊዜ ለተጠቃሚው ተንከባካቢዎች ጊዜያዊ ፋታ የሚሰጡ አገልግሎቶች ናቸው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለልጆች፣ ለወጣቶች እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***የተመላላሽ ሕመምተኛ የአእምሮ ጤና ማዕከል ወይም የግል የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪ፦*** *የተመላላሽ ሕመምተኞች የሕክምና አገልግሎቶች የስነ አእምሮ ወይም የክሊኒክ ግምገማና ምርመራን፣ የግል ቴራፒን፣ በቡድን የሚደረግ ቴራፒን፣ የቤተሰብ ቴራፒን፣ ለቤተሰብ የሚሰጥ የስነ አእምሮ ትምህርትን ወይም የመድሃኒት አስተዳደርን ሊጨምሩ ይችላሉ። ይህ አገልግሎት የሚሰጠው ፈቃድ ባላቸው የተመላላሽ ሕመምተኞች የአእምሮ ጤንነት ማዕከሎች* (OMHCs) *ወይም ተገቢው ቦርድ ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት በሰጣቸው በግል የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች በኩል ነው።*

- ***የስነ አእምሮ ማገገሚያ መርሃ ግብር (PRP)፦*** *የ*PRP *አገልግሎቶች የተዘጋጁት ከባድና ቀጣይ የአእምሮ ሕመም* (SPMI) *ያላቸው ተጠቃሚዎች እንዲሻላቸውና ራስን ችሎ መኖርንና ማህበራዊ ችሎታዎችን እንዲሁም ለራስ መጠንቀቅን፣ ሕመም ማስተዳደርን፣ ኑሮንና የማህበረሰብ ተሳትፎ እንደገና እንዲያገኙ፣ እና ያሉትን አገልግሎቶች በመጠቀም ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ለማስቻል ነው። አገልግሎቶች የሚሰጡት በአገልግሎት መስጫ ማዕከል ውስጥ ወይም ተጠቃሚው የማህበረሰብ ኑሮ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችለው አካባቢ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለልጆች፣ ለወጣቶች እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***የመኖሪያ ቤት ውስጥ ማገገሚያ መርሃ ግብር* (RRP)**: *የ*RRP *አገልግሎቶች ከባድና ቀጣይ የአእምሮ ሕመም* (SPMI) *ያላቸው፣ ጥልቀት ያለው ማገገም እና በተሰናዳ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተጠቃሚዎች የተዘጋጁ ናቸው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ የሽግግር ዕድሜ ላይ ላሉ ወጣቶች* (TAY) *እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***ማህበረሰብ ውስጥ የሚደረግ ሕክምና/ተንቀሳቃሽ ሕክምና፦*** *ማህበረሰብ ውስጥ የሚደረግ ሕክምና/ተንቀሳቃሽ ሕክምና ጥልቀት ያለው ማህበረሰብ ውስጥ ለከባድና ቀጣይ የአእምሮ ሕመም* (SPMI) *ላለባቸውና ቤት አልባ ወይም ሌሎች የተመላላሽ ሕክምና ላልሰራላቸው ግለሰቦች የሚሰጥ ሕክምና፣ ማገገሚያና ድጋፍ ነው። አገልግሎቶች የሚሰጡት ተንቀሳቃሽ የሆነ ቡድን ተጠቃሚው ያለበት ድረስ በመሄድ ነው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለልጆች፣ ለወጣቶች እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***የጉዳይ አስተዳደር፦*** *የጉዳይ አስተዳደር አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ማግኘት እንዲችሉና ተጨማሪ አስፈላጊ የሕክምና፣ ማህበራዊ፣ የገንዘብ ጥቅማጥቅም፣ ምክር፣ ትምህርት፣ መኖሪያና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ማግኘት እንዲችሉ በቤት ወይም በማህበረሰብ ውስጥ የሚቀርቡ ናቸው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለልጆች፣ ለወጣቶች እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***ድጋፍ ያለው ኑሮ፦*** *ድጋፍ ያለው ኑሮ ከባድና ቀጣይ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው* (SPMI)*፣ እራሳቸው በመረጡት ቦታ የግል ድጋፎች እያገኙ መኖር ለሚችሉ ተጠቃሚዎች የማገገሚያ እና የድጋፍ አገልግሎቶች ይሰጣል። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለ*TAY *እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***ድጋፍ ያለው ሥራ፦*** *ተወዳድረው ሥራ ማግኘት ላልቻሉ፣ ሥራው ለተቋረጠባቸው ወይም አጫጭር ለሆነባቸው ከባድ የአእምሮ ሕመም* (SMI) *ወይም የስሜት መቃወስ ላለባቸው ተጠቃሚዎች ድጋፍ ያለው ሥራ* (SE) *አገልግሎቶች የሥራ ማጎልበትና ምደባ፣ የሥራ መግራት እና ቀጣይ ሥራ ያቀርባል። እነዚህ የግል አገልግሎቶች ብቃት ያላቸው ተጠቃሚዎች ከማህበረሰብ ውስጥ በተቀላቀለ አካባቢ ውስጥ፣ ተወዳድረው ከፍላጎታቸውና ከችሎታዎቻቸው ጋር አብሮ የሚሄድ ሥራ ለመምረጥ፣ ለማግኘት፣ ለማቆየት ወይም ለመሾም እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለ*TAY *እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***የመኖሪያ ቤት ውስጥ ችግር፦*** *የመኖሪያ ቤት ውስጥ ችግር አገልግሎቶች ለአጭር ጊዜ የሚሰጡ ጥልቀት ያላቸው ሆስፒታል ውስጥ ሳይሆን፣ በማህበረሰብ ውስጥ ያለ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚሰጡ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ሲሆኑ ተጠቃሚው ሆስፒታል ውስጥ መግባት እንዳይኖርበት ለየት ያለ የአእምሮ ሕክምና እንዲያገኝ ወይም በሆስፒታል ውስጥ መቆየት ያለበትን ጊዜ አጠር ያለ እንዲሆን የሚያደርጉ አገልግሎቶች ናቸው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለልጆች፣ ለወጣቶች እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

- ***ከአእምሮ ጤና ጋር የተያያዙ የላቦራቶሪ አገልግሎቶች፦*** *ለሕክምና የሚያስፈልጉ ምርመራዎችንና ፈቃድ ባላቸው ላቦራቶሪዎች የሚደረጉ አስፈላጊ ምርመራዎችን ይጨምራል። እነዚህ ላቦራቶሪዎች ከአእምሮ ሕመሙ ጋር የተያያዘ የሜዲኬድ አገልግሎት ሰጪ ቁጥር ያላቸውና* PMHS *ውስጥ ያሉ አገልግሎት ሰጪዎች የሜዲኬድ ብቃት ላላቸው ተጠቃሚዎች የሚሰጡት ናቸው። ይህ የአገልግሎት ደረጃ ለሜዲኬድ ብቃት ላላቸው ልጆች፣ ወጣቶችና አዋቂዎች የሚሰጥ ነው።*

***አገልግሎቶች ማግኘት***

PMHS *ውስጥ ያሉት አገልግሎቶች በሙሉ ብቃት ላላቸውና ለሕክምና አስፈላጊ ነው ተብሎ ሲወሰን የሚሰጡ ናቸው። የአእምሮ ጤና ሕክምና አገልግሎቶች ለማግኘት በቀን* 24 *ሰዓት፣ በሳምንት* 7 *ቀን የነጻ ስልክ ጋር መደወል ይቻላል።*

> ***የአገልግሎቶችች አስተዳደር ቢሮ*** **(ASO)** *ጋር ይደውሉ፦*
> 1-800-888-1965

***ለሌሎች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች በሙሉ፣ ድጋፍ ያለው ሥራን ወይም በአውራጃዎ ውስጥ የሚገኙ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ ጨምሮ፣ አውራጃዎ ውስጥ የሚገኝ የክልልዎ ዋና አገልግሎት ድርጅት ጋር ይደውሉ።***

**Allegany County Core Service Agency**
Allegany Co. Mental Health System's Office
P.O. Box 1745
Cumberland, Maryland 21501-1745
**ስልክ፦** 301-759-5070
**ፋክስ፦** 301-777-5621
**ኢሜል፦** mhso@hereintown.net

**Anne Arundel County Core Service Agency**
Anne Arundel County Mental Health Agency
Box 6675, MS 3230
1 Truman Parkway, Suite 101
Annapolis, Maryland 21401
**ስልክ፦** 410-222-7858
**ፋክስ፦** 410-222-7881
**ኢሜል፦** mhaaac@aol.com

**Baltimore City Core Service Agency**
Baltimore Mental Health Systems, Inc.
201 East Baltimore Street, Suite 1340
Baltimore, Maryland 21202
**ስልክ፦** 410-837-2647
**ፋክስ፦** 410-837-2672

**Baltimore County Core Service Agency**
Bureau of Mental Health of Baltimore County Health Department
6401 York Road, Third Floor
Baltimore, Maryland 21212
**ስልክ፦** 410-887-3828
**ፋክስ፦** 410-887-4859

**Calvert County Core Service Agency**
P.O. Box 980
Prince Frederick, Maryland 20678
**ስልክ፦** 410-535-5400
**ፋክስ፦** 410-535-5285

**Carroll County Core Service Agency**
290 South Center Street, P.O. Box 460
Westminster, Maryland 21158-0460
**ስልክ፦** 410-876-4440
**ፋክስ፦** 410-876-4929

**Cecil County Core Service Agency**
401 Bow Street
Elkton, Maryland 21921
**ስልክ፦** 410-996-5112
**ፋክስ፦** 410-996-5134

**Charles County Core Service Agency**
Charles County Human Services Partnership
P.O. Box 2150,
6 Garrett Avenue
LaPlata, Maryland 20646
**ስልክ፡** 301-396-5239
**ፋክስ፡** 301-396-5248

**Frederick County Core Service Agency**
Mental Health Mgmt Agcy of Frederick County
22 South Market Street, Suite 8
Frederick, Maryland 21701
**ስልክ፡** 301-682-6017
**ፋክስ፡** 301-682-6019

**Garrett County Core Service Agency**
1025 Memorial Drive
Oakland, Maryland 21550-1943
**ስልክ፡** 301-334-7440
**ፋክስ፡** 301-334-7441
**ኢሜል፡** gccsa@dhmh.state.md.us

**Harford County Core Service Agency**
Office on Mental Health
206 South Hays Street, Suite 201
Bel Air, Maryland 21014
**ስልክ፡** 410-803-8726
**ፋክስ፡** 410-803-8732

**Howard County Core Service Agency**
Howard County Mental Health Authority
9151 Rumsey Road, Suite 150
Columbia, Maryland 21045
**ስልክ፡** 410-313-7350
**ፋክስ፡** 410-313-7374
**ኢሜል፡** hcmha@hcmha.org

**Mid-Shore Core Service Agency**
(**ካሮላይን፣ ዶርቼስተር፣ ኬንት፣ ክዊን አን እና ታልበት ካውንቲዎችን ያካትታል**)
Mid-Shore Mental Health Systems, Inc.
8221 Teal Drive, Suite 203
Easton, Maryland 21601
**ስልክ፡** 410-770-4801
**ፋክስ፡** 410-770-4809

**Montgomery County Core Service Agency**
Department of Health & Human Services, Montgomery County Government
401 Hungerford Drive, 5th Floor
Rockville, Maryland 20850
**ስልክ፡** 240-777-1400
**ፋክስ፡** 301-279-1692

**Prince George's County Core Service Agency**
Prince George's Co. Dept. of Family Services
Mental Health Authority Division
5012 Rhode Island Avenue, Room 114
Hyattsville, Maryland 20781
**ስልክ፡** 301-985-3890
**ፋክስ፡** 301-985-3889

**St. Mary's County Core Service Agency**
St. Mary's County Dept. of Human Services
23115 Leonard Hall Drive, PO Box 653
Leonardtown, Maryland 20650
**ስልክ፡** 301-475-4200, Ext. 1680
**ፋክስ፡** 301-475-4000

**Wicomico Somerset County Regional Core Service Agency**
108 East Main Street
Salisbury, Maryland 21801
**ስልክ፡** 410-543-6981
**ፋክስ፡** 410-219-2876

**Washington County Core Service Agency**
Washington County Mental Health Authority
339 E. Antietam Street, Suite #5
Hagerstown, Maryland 21740
**ስልክ፡** 301-739-2490
**ፋክስ፡** 301-739-2250

**Worcester County Core Service Agency**
P.O. Box 249
Snow Hill, Maryland 21863
**ስልክ፡** 410-632-1100
**ፋክስ፡** 410-632-0065
**ኢሜል፡** worcsa@dmv.com

## 4. የሰው ኃይል ልማትና የአዋቂ ትምህርት ክፍል

የሰው ኃይል ልማትና የወጣት አገልግሎት ክፍል ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 21 ያሉ ወጣቶች/ወጣት አዋቂዎች የትምህርትና የሥራ ዓላማዎቻቸውን እንዲፈጽሙ የሚረዱ መርሃ ግብሮችንና አገልግሎቶችን ያቀርባል። ወጣቶችና ወጣት አዋቂዎች ትምህርት ላይ ስኬታማ ለመሆን፣ ሥራ ማግኘት የሚያስችሉ ችሎታዎችንና የኑሮ ችሎታዎችን የሚያዳብሩ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ። የሰው ኃይል ልማት ቢሮ ለወጣቶች በሙሉ የአእምሮ እና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ወጣቶች ጨምሮ የሥራና የስልጠና አገልግሎቶች የሚሰጡ የተለያዩ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ መርሃ ግብሮችን ይደግፋል። የሰው ኃይል ልማት ማዕከሎች ወጣት አዋቂዎች ሥራ እንዲፈልጉ፣ ሙያ እንዲመርጡ እና እንዲቀይሩ ወይም አዳዲስ ችሎታዎች እንዲያዳብሩ የተፈጠሩ ናቸው። የሙያ ምክር፣ ስልጠና፣ ኮምፒዩተር መጠቀሚያ እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች በክልሉ የሰው ኃይል ልማት ቦርዶች እና በዋን ስቶፕ ማዕከሎች በኩል ይቀርባሉ። አገልግሎቶችን ለማግኘት ለመመዝገብ ወጣት አዋቂዎች የክልሉን የሰው ኃይል ልማት ማዕከል መጎብኘት አለባቸው።

## የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የጉዳት ድጋፍ አገልግሎቶች

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት መሸጋገር ከባድ ሊሆን ይችላል። ልክ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የሚሆነው? ከየት ነው የምጀምረው? እርዳታ ካስፈለገኝ የት ነው የምሄደው? ድጋፎቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የነበሩት ዓይነት ናቸው? የድጋፍ ዕቅድ ማውጣት ላይ ወላጆቼ ይሳተፋሉ? የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ ለመሄድ ሲዘጋጁ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች እነዚህን ይመስላሉ። ከዚህ በታች ያለው መረጃ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። በዩ ኤስ ትምህርት መምሪያ የተዘጋጀም የዕቅድ ማውጫ መምሪያ አለ። ኢንተርኔት ላይ በሚከተለው አድራሻ ይገኛል፦ www.ed.gov።

## በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኮሌጅ መካከል ያሉት ልዩነቶች

- **የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) አሁንም ይኖረኛል?**

  አይ። በ2004 ዓ.ም. የወጣው የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ሕግ (IDEA) የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ IEP እንዲኖረው ያስገድዳል። ሆኖም IDEA ኮሌጆችን፣ የንግድ ትምህርት ቤቶችን ወይም ዩኒቨርሲቲዎችን አይመለከትም። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በሌሎች የፌዴራል ሕጎች፣ እንዲሁም የአእምሮ እና የአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካኖች (ADA) እና የሙያ ማሻሻያ ሕግ አንቀጽ 504 ግዛት ሥር ያሉ ናቸው። የኮሌጆች፣ የንግድ ትምህርት ቤቶች፣ እና የዩኒቨርሲቲዎች ኃላፊነት ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ኃላፊነቶች በጣም ይለያሉ። ዋናው ልዩነት ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከወጣቱ ጋር እንጂ ከወላጅ ጋር አይደለም የሚሠሩት። ወጣቱ የኮሌጅ ተማሪ ሲሆን ይበልጥ ከባድ ኃላፊነቶች ይኖሩታል። እነዚህ ሕጎች አገልግሎት መጠየቅና ጉዳቱን በተመለከተ ተገቢውን ሰነድ ማቅረብ የወጣቱ ኃላፊነት ያደርጉታል። ወጣቱ በሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ መሆን አለበት።

- **ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩኝን ዓይነት መነናደዎች አገኛለሁ?**

  ይህ ላይሆን ይችላል። IEPው ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አይሸጋገርም። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ምን ዓይነት መሰናዶዎች ተማሪው እንደሚያገኝ የሚወስነው ሰነዱ ከታየና መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ነው።

## ኮሌጅ ውስጥ አገልግሎቶች ማግኘት

- **አገልግሎቶች ለማግኘት የት ነው የምሄደው?**

  እያንዳንዱ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች የሚረዱ ግለሰቦች አሏቸው። እነዚህ ግለሰቦች የጉዳት ድጋፍ አገልግሎቶች ቢሮ (DSS) ውስጥ ይገኛሉ። ትምህርት ነክ መሰናዶዎች እና/ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ለማግኘት ወጣቱ በመጀመሪያ ራሱን ለDSS ቢሮ ማሳወቅ አለበት። ስለሚያስፈልጉት ድጋፎች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱን ማነጋገር የወጣቱ ኃላፊነት ነው።

- **አገልግሎቶች መቼ ልጠይቅ?**

  ወጣቱ ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ በማንኛውም ጊዜ መሰናዶዎች መጠየቅ ቢችልም የትምህርት ሰሚስተሩ በተጀመረ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከ DSS ቢሮ ጋር ቀጠሮ ቢይዝ ይመረጣል። አገልግሎቶችና መሰናዶዎች ማዘጋጀት ጊዜ የሚወስድ ነገር ነው። አንዳንድ ትምህርት ነክ መሰናዶዎች ከሌሎች ይበልጥ ጊዜ ሊፈጁ ይችላሉ። መሰናዶዎች ምንጊዜም ወደኋላ ተመልሰው ሊደረጉ አይችልም። ወጣቱ ትምህርት ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ እስኪፈጠር መጠበቅ የለበትም።

- **ምን ዓይነት ሰነድ ማቅረብ አለብኝ?**

  ትምህርት ቤቶች ለሰነድ አቀርቦት ተገቢ መስፈርቶች ያስቀምጣሉ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከሌሎች ትምህርት ቤቶች የበለጠ ሰነድ ሊጠይቁ ይችላሉ፣ ሆኖም ትምህርት ቤቶች በሙሉ በተገቢው ባለሙያ የተዘጋጀ ሰንድ ወጣቱ እንዲያቀርብ ይጠይቃሉ። ሰነዱን ለማግኘት የሚከፈሉት ሒሳቦች በሙሉ የወጣቱ ኃላፊነት ይሆናሉ። የሰነዱ ዋና ክፍሎች ይሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- *ጉዳቱን የሚገልጽ ምርመራ።*
- *የተደረገው የምርመራ ዓይነት።*
- *በትምህርት እና በመኖሪያ ሁኔታ አካባቢ አሁን ያሉት እንቅፋቶች።*
- *የጉዳቱ ሂደት ወደፊት እንዴት ይሆናል ተብሎ እንደሚጠበቅ የሚናገር መግለጫ።*
- *የአሁን እና ያለፉት መሰናዶዎች፣ አገልግሎቶች እና/ወይም መድሃኒቶች ምን እንደሚመስሉ መግለጫ።*
- *ለመሰናዶዎች፣ ለማሻሻያ መሳሪያዎች፣ ለረዳት አገልግሎቶች፣ ለማሻሻያ ዕቅዶች እና/ወይም ድጋፍ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሐሳቦች።*

***አንድ IEP ከዚህ ቀደም የሠሩትን አገልግሎቶች ለማወቅ ቢረዳም፣ ባብዛኛው ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቂ መረጃ አይደለም።***

***ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ መሰናዶዎች ማግኘት***

- ***ምን ዓይነት መሰናዶዎች ይቀርባሉ?***

*መሰናዶዎች የትምህርት መስፈርቶች ላይ የሚደረጉ ማሻሻሎች ሲሆኑ፣ እነዚህም የሚደረጉት የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ወጣቶች ከሌሎች እኩል መሳተፍ እንዲችሉ ነው። ተገቢ መሰናዶዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦*

- *ፈተናዎች ላይ ረዘም ያለ ጊዜ መስጠት*
- *በልዩ ዓይነት መልክ የቀረቡ መጽሐፍቶች*
- *መስማት ለሚሳናቸው የእጅ ቋንቋ አስተርጓሚዎች*
- *የስክሪን አንባቢዎች*
- *ድምጽ አዋቂ መሳሪያ*
- *ሌላ ዓይነት ረዳት ቴክኖሎጂ*

***የDSS ቢሮ ከወጣቱ ጋር አብሮ በመሥራት ተገቢዎቹን መሰናዶዎች ያዘጋጃል። ትምህርቱን በጣም የሚያስቀይር ከሆነ መሰናዶው ሊቀርብ አይችልም። አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶችን ይለፈኝ ብሎ መፈረም አይቻልም። የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ለመመረቅ የትምህርት ዘርፉን መስፈርቶች የማሟላት ግዴታ አለባቸው።***

***በተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፦***

***የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ላለባቸው ሥራ ፈላጊዎች ሥራ ነክ መረጃ የያዘ ድህረ ገጽ፦***
www.dllr.state.md.us/employment/disabilities.shtml

***የክልሉ ዋን ስቶፕ ማዕከሎች ዝርዝር፦***
www.dllr.state.md.us/county/

# በሽግግር ዕቅድ ማውጣት ላይ ወላጅ የሚጫወተው ሚና

## ስለ ሽግግር ለመወያየት ቤተሰቦች በምን ዓይነት ሁኔታ መዘጋጀት ይችላሉ?

ወላጆች ሽግግርንና ልጆቻቸው ሊያስፈልጓቸው የሚችሉትን አገልግሎቶች ለመወያየት ለመዘጋጀት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- ልጃቸው አሁን የሚወዳቸውን እንቅስቃሴዎችና ከትምህርት በኋላ ምን ማድረግ እንደሚወድ ለማወቅ ልጃቸውን ማነጋገር። የሽግግር ዕቅድ በሙሉ የተመሠረተው በተማሪው ፍላጎትና ምርጫ ላይ ተመርኩዞ ነው።
- ልጁ ለራሱ መቀም የሚያስችሉትን ችሎታዎች እንዲያዳብር ከትምህርት ቤቱ ጋር አብረው ይሥሩ።
- እዚህ መምሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን ድርጅቶች ይወቁ።
- የልጃቸውን የወደፊት ሕልም ማዳበርና መደገፍ።
- ልጃቸው ለIEP የሽግግር ቡድን ስብሰባ እንዲዘጋጅ ትምህርት ካለቀ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ በተመለከተ ሓሳቦቹን እንዲሰበስብና እንዲያስተካክል ማገዝ።
- ለቤት የሚሆን የሽግግር መረጃ የያዘ ሰነድ አዘጋጅቶ መያዝ። ይህ የቤት ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይችላል፦
    - ☐ የልጁ የቅርብ IEPዎች፣
    - ☐ የአዋቂ አገልግሎት ድርጅት መገናኛ መረጃ፣
    - ☐ የልጁ መውጫ ሰነድ (በምረቃ ጊዜ የሚገኝ)፣
    - ☐ የልጁ የተጨማሪ ሴክዩሪቲ (SSI) እና የሜዲኬድ መረጃ (የሚመለከተው ከሆነ)፣
    - ☐ የልጁ ግምገማዎችና ምርመራዎች ሁሉ ግልባጮች፣
    - ☐ የድርጅት ማመልከቻ ማስገቢያ የጊዜ ገደቦች፣ እና
    - ☐ ከድርጅቶች ጋር የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች

# በሽግግር ዕቅድ ማውጣት ላይ ተማሪው የሚጫወተው ሚና

*የሽግግር ዕቅድ ማውጣት የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ለራሳቸው ዓላማዎች እንዲያወጡና እነዚህን ዓላማዎች መፈጸም እንዲችሉ በትምህርት የተመሠረቱ መርሃ ግብሮችን እንዲያዘጋጁ ተማሪዎችን ይረዳል። የሽግግር ዕቅድ ማውጣት ለተማሪው ስለሆነ የእርሱ/የእርሷ ሐሳብ የዕቅድ ማውጫ ሂደቱ ላይ ካልቀረበ ስኬታማ አይሆንም። ለሂደቱ ለመዘጋጀት ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፦*

- *ፍላጎቶቻቸውን ከወላጆቻቸው ጋር መወያየት (አሁን ማድረግ ደስ የሚላቸውን እንጂ በግድ ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ያላቸውን ዕቅድ ሳይሆን)፤*
- *የሥራ መስኮችን መመራመር፤*
- *የ IEP ቡድን ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ ለራሳቸው ለመቆም መዘጋጀት (ከወላጆች ጋር ወይም ከአስተማሪዎች ጋር በቅድሚያ ለዚህ መለማመድ)፤ እና*
- *የ IEP ቡድን ስብሰባ ላይ ጥያቄዎች መጠየቅ (ለትምህርት እንቅፋት የሆነ ጉዳት አለኝ ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው?  ማንበብ እንደሚያስቸግረኝ ለሥራ ቦታ መናገር አለብኝ?)*

# የሽግግር ሂደት፦ ከድርጅት ጋር ማያያዝ

ልጅዎ የከፍተኛ ደረጃ የሥራ፣ የትምህርት፣ የስልጠና እና ራስን ችሎ የመኖር (የሚመለከተው/ታት ከሆነ) ዓላማዎችን ለማሳካት የአዋቂ አገልግሎቶች ያስፈልጉት/ጓት ይሆናል። ስለዚህ መዘግየት እንዳይፈጠር ትምህርት ቤት ከመልቀቁ/ቋ በፊት አስፈላጊውን ግንኙት መፍጠር አለብዎት። ፈቅድዎ ከሆነ የትምህርት ቤት ወኪል ልጅዎን ከተገቢው አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ያገናኝዋል/ያገናኛታል። ማመልከቻውን መሙላት የእርስዎ ኃላፊነት ነው። አዋቂ የሆነው/የሆነችው ልጅዎ የሚያስፈልጉት/ጓት አገልግሎቶች እንዲደርሰው/እንዲደርሳት ማድረግ የራሱ/የራሷ ኃላፊነት ነው።

የሽግግር ዕቅድ ማውጫ መምሪያ ስለ አዋቂ አገልግሎቶች መረጃ ያቀርባል። መምሪያው ድርጅቶችን ለመጠቀም መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች እና ልዩ የማያያዝ ሂደቶችን በተመለከተ መረጃ ይዟል። ይህ መረጃ እርስዎና ልጅዎ የሽግግር ሂደቱንና ከአዋቂ አገልግሎቶች ጋርይ የማያያዝ ሂደቱን ስትጀምሩ ይጠቅማችኋል።

የሽግግር ዕቅድ ማውጫ መምሪያውን ማንበብ ከድርጅት ጋር ለመያያዝ የመጀመሪያ ደረጃ ነው። መምሪያው ትክክለኛውን የእርዳታ ድርጅት ለመምረጥ የሚያስችል መረጃ ያቀርባል። የልጅዎ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ስልክ ቁጥርና ሌላ ለማመልከቻው የሚያስፈልግ መረጃ ይሰጥዋችኋል።

የሽግግር ዕቅድ ማውጫ መምሪያ ሲደርስዎት ከአዋቂ አገልግሎት ድርጅቶች ጋር የመያያዝ የመጀመሪያ ደረጃውን ጀመሩ ማለት ነው። የዚህ መምሪያ መሰጠት ከሽግግር ዕቅድ ሂደት ውስጥ አንዱ ነው፣ ይህን ቅጽ ሲፈርሙም መምሪያው እንደደረስዎት ያረጋግጣሉ።

የተማሪ ስም፦ ______________________________

የተማሪ ፊርማ፦ ______________________________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ፦ ______________________________

ቀን፦ ______________________________

የክልሉ ትምህርት ሥርዓት፦

______________________________

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services
200 West Baltimore Street, 9th Floor
Baltimore, Maryland 21201
www.MarylandPublicSchools.org